**ኖቬምበር 20/2018 QuickNotes**

## ለ2019-2020 የትምህርት አመት አስቀድማችሁ እቅድ/ፕላን አድርጉ

የትምህርት ቦርድ ለ 2019-2020 የትምህርት ዓመት የሚሆን ቀን መቁጠሪያ/ካለንደር ወስኗል። የትምህርት አመቱ ማክሰኞ፣ መስከረም 3/2019 ላይ ይጀምራል፣ እና የመጨረሻው የትምህርት ቀን ሰኞ ሰኔ 15/2020 እንደሚሆን መርሃ ግብር ተይዟል። የቀን መቁጠሪያው 182 የትምህርት ቀናት፣ 10 ቀን የፀደይ/ስፕሪንግ ዕረፍት፣ በእያንዳንዱ ሴሚስተር መካከል አንድ ሙሉ ቀን የእቅድ እና የሙያ ዕድገት ቀናትን ያካትታል።

በ Governor Larry Hogan እ.ኤ.አ. ኦክቶበር 31/2016 የተሰጠ እና (በግንቦት 31/2016 የተሻሻለው) የተለመደው አጠቃላዩ የትምህርት አመት የጊዜ ማእቀፍ የሥራ መመሪያ ለ2019-2020 የትምህርት አመትም ይቀጥላል። የቀን መቁጠሪያ/ካላንደሩ የተዘጋጀው በስቴት ህግ ከተደነገገው የት/ቤት መዝጊያ ሁነቶች ጋር ለማስማማት፣ ከስቴት ሱፐርኢንተንደንት የተሰጠ የአስቸኳይ ጊዜ/ሁኔታ የማካካሻ ቀናት መመሪያ፣እና በሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ማህበር/Association ኮንትራት የሚፈለገዉን በቅድሚያ የሚለቀቁባቸውን ቀናት ለመተግበር ነዉ።

በዚህ አመት MCPS ባልተጠበቀ ሁኔታ በወሰደው እርምጃ ዳሰሳ ወስዶ ከ MCPS ማህበረሰብ ውስጥ ከእያንዳንዱ ሰራተኛ እና ቤተሰብ ጋር ለየብቻ ግንኙነት አድርጓል። የ 2019-2020 የቀን መቁጠሪያ የዚህ የዳሰሳ ጥናት ውጤቶችን እና ግብረመልሶችን፣ እንዲሁም ከ MCPS የውስጥ ሠራተኞች ቡድን እና ዘጠኝ የተለያዩ የማህበረሰብ ቡድኖችን የሚወክሉ የውጭ ፓርቲዎች የትኩረት ቡድን ግብረ መልስ ውጤት ነው።

የቀን መቁጠሪያ/ካላንዳር ለመመልከት **እዚህ** ጠቅ/ክሊክ ያድርጉ።

## ሪፖርት ካርዶች ኖቬ. 20 ይሰራጫሉ

ወላጆች፣ የልጅዎ የመጀመሪያ ሪፖርት ካርድ ወደ ቤት ይላካል **ማክሰኞ፣ ኖቬምበር 20** ሪፖርት ካርዶች በሚከተሉት ቀናትም ወደ ቤት ይላካሉ፡-

- ፌብሯሪ 6
- ኤፐረል 19
- ጁን 27

በመካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ልጆች ያሏቸው ወላጆች የልጆቻቸውን ውጤቶች ዓመቱን በሙሉ በ myMCPS parent portal መከታተል ይችላሉ። የነኛ ደረጃ ተማሪ ያላቸው ቤተሰቦች የልጆቻቸውን ሪፖርት ካርድ ውጤት እና ትምህርት የተከታተሉበትን ሁኔታ ለማየት ይችላሉ።

ሪፖርት ካርዶች
MyMCPS

**እጅግ የላቀ(ች) መምህር፣ የድጋፍ ሠራተኛ ወይም ርእሰመምህር ያውቃሉ?**

ሽልማቶች የሚሰጥበት ወቅት ደርሷል! ከሐሙስ ኦክቶበር 18 ጀምሮ ልዩ አስተዋጽኦ ያደረጉ መምህራን፣ ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች እና ርእሰ መምህራንን እውቅና-ክብር ለመስጠት ለተለያዩ ውድድሮች ጥቆማ ክፍት ነው። እነዚህም የሚከተሉት ናቸው—

**ማሪን ግሪንብላት በማስተማር ክህሎት የላቀ የመምህር ሽልማት/"The Marian Greenblatt Excellence in Education Master Teacher Award"** ከሙዋዕለህፃናት እስከ 12ኛ ክፍል ድረስ ከሚያስተምሩ የሙሉ-ጊዜ መምህራን ውስጥ የተማሪዎችን የክንዋኔ ክፍተት በማጥበብ ለስኬት እንዲበቁ በማስቻል ወደር የሌለው ውጤት ያስመዘገቡ ለሦስት መምህራን ሽልማት ይሰጣል። ከዋነኞቹ የ "Master Teacher Award" ተሸላሚ መምህራን አንደኛው የ MCPS የአመቱ መምህር በመሆን ተመርጦ/ጣ የትምህርት ቤ/ት ድስትሪክቱን በመወከል ለሜሪላንድ ስቴት "የዓመቱ መምህር" ሽልማት ለመወዳደር ይቀርባል/ትቀርባለች እና በአገር አቀፍ ደረጃ የዓመቱ መምህር/ት ለመሆንም ይችል/ትችል ይሆናል። ለያንዳንዱ ደረጃ- ለኤሌሜንታሪ፣ ለመካከለኛ እና ለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት - አንድ የሽልማት አሸናፊ ይኖራል። እያንዳንዳቸው የ$2,000 የገንዘብ ሽልማት ይቀበላሉ። ተጨማሪ መረጃ **እዚህ** ይገኛል። **ቀነ ገደብ:- አርብ፣ ጃንዋሪ 11/2019**

**The Marian Greenblatt Excellence in Education Rising Star Teacher Award/በምጥቀት ላይ የሚ(ምት)ገኝ ኮከብ መምህር ሽልማት** ከምዋእለ ህፃናት እስከ 12ኛ ክፍል የተማሪ ስኬት በማራመድ ከፍተኛ ውጤት ላስመዘገበ/ች የአንደኛ-፣
ሁለተኛ-፣ ሶስተኛ- ወይም ለአራተኛ ዓመት ቋሚ መምህር እውቅና ይሰጣል። መምህሩ/ሯ ለተማሪዎች፣ ሰራተኞች፣ ለወላጆች እና ለማህበረሰብ ፕሮፌሽናል የትምህርት ማህበረሰብ አስተዋፅኦ ያደርጋል/ታደርጋለች። አሸናፊው/ዋ $1,000 የገንዘብ ሽልማት ያገኛል/ታገኛለች። የበለጠ መረጃ/ኢንፎርሜሽን ይገኛል **እዚህ**። **የቀነ ገደብ:- ዓርብ፣ ጃኑዋሪ 11/2019**

**የዋሽንግተን ፖስት/The Washington Post የዓመቱ መምህር(ት) ሽልማት/Teacher of the Year Award (ከዚህ በፊት አግነስ መየር የላቀ መምህር ሽልማት/formerly the Agnes Meyer Outstanding Teacher Award)**:-የዋሽንግተን ፖስት/The Washington Post የዓመቱ መምህር(ት) ሽልማት እውቅና የሚሰጠው ከቅድመ መዋለ ህፃናት እስከ 12ኛ ክፍል የተማሪዎችን የመማር ፍላጎታቸውን በማጎልበት ለስኬታማነት ለሚያዘጋጁ የሙሉ-ጊዜ መምህር(ት) ነው። እያንዳንዱ/ዷ ተሰያሚ ቢያንስ የአምስት አመት የማስተማር ተሞክሮ እንዲኖረው ያስፈልጋል፣ ከነዚህም ሶስቱ MCPS ውስጥ መሆን አለባቸው። መምህሩ/ሯ የተማሪዎች ግላዊ ፍላጎቶች መገንዘብ፣ ችሎታዎቻቸውን ማበረታታትና የግል ክብራቸውን መንከባከብ በተጨማሪ ይገባዋል/ታል። እሱ ወይም እሷ የርእሰ ነገሩ ጥልቅ እውቀት እንዲያ(ድታ)ሳይ እና ከተማሪዎች ጋር በውጤታማነት የመጋራት ችሎታ ይኖረዋ(ራታ)ል። ተሰያሚው/ዋ ከስራ ጓዶቹ/ቿ እና ከህብረተሰቡ ጋር የትብብር ግንኙነት ይንከባከባል/ትንከባከባለች እናም የላቀ የአመራር ችሎታ ያሳያል/ታሳያለች። አሸናፊው/ዋ ዋንጫ፣ $7,500 የገንዘብ ሽልማት እና ታሪካቸው በዋሽንግተን ፖስት/The Washington Post ላይ ይወጣል። **የጊዜ ገደብ:- 4 p.m. ዓርብ፣ ጃኑዋሪ 4/2019**

**The Washington Post Principal of the Year Award/የአመቱ ርእሰመምህር ሽልማት (ቀድሞ Distinguished Educational Leadership Award ተብሎ የሚታወቅ)**፡- ይህ ሽልማት ወደር የሌለው የትምህርት አካባቢ ለመፍጠር ከቀን-ወደ-ቀን የስራ ቦታቸው ከሚጠይቀው የሚሻገሩ ርእሰመምህራንን እውቅና ይሰጣል። እነዚህን ሽልማቶች ሲያበረክት፣ የዋሽንግተን ፖስት/The Washington Post Company Educational Foundation/የትምህርት መሠረት በት/ቤት የአመራር/አስተዳደራዊ ጥበብን ለማበረታታት እና በዋሺንግተን ሜትሮፖሊታን አካባቢ ለትምህርት መሻሻል በሰፊው ለማበርከት ተስፋ ያደርጋል። ጥቆማዎች በመምህራን፣ በተማሪዎች፣ በቀድሞ ተማሪዎች፣ በወላጆች፣ በአስተዳዳሪዎች፣ ወይም በሰፊው ማህበረሰብ ሊቀርቡ ይችላሉ። አሸናፊው/ዋ ዋንጫ፣ $7,500 የገንዘብ ሽልማት እና ታሪካቸው በዋሽንግተን ፖስት/The Washington Post ላይ ይወጣል። **የጊዜ ገደብ፡- 4 p.m. ዓርብ፣ ጃኑዋሪ 4/2019**

**The Shirley J. Lowrie Thank You for Teaching Award**፡-The Shirley J. Lowrie "Thank You for Teaching" ሽልማት ለማስተማር ሙያ ጥልቅ ቁርጠኛነት ያላቸው የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራንን አክብሮት/እውቅና ይሰጣል። እነዚህ የኤሌመንታሪ ት/ቤት መምህራን፣ ከቅድመ-ሙዋእለ ህፃናት እስከ 5ኛ ክፍል፣ በየእለቱ ከተማሪዎች ጋር በመማርያ ክፍል አብረው መስራት አለባቸው፣ በትምህርቱ ርእስ ሰፊ እውቀት እንዳላቸው ያሳያሉ፣ እና ያንን የትምህርት ርእስ በሚያመረቃ ሁኔታ ለተማሪዎች ማስተላለፍ አለባቸው። ተጠቋሚው/ዋ፣ ተማሪዎች ስኬታማ ለመሆን የሚያስፈልጋቸውን ድጋፍ ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ፣ ተጨማሪ ጥረት የሚያ(ምታ)ደርግ መምህር መሆን አለበ(ባ)ት። **የጊዜ ገደብ፡- 4 p.m. ዓርብ፣ ጃኑዋሪ 4/2019**

**The Superintendent's Annual Mark Mann Excellence and Harmony Award**፡-የተመሠረተው በ 1991 ሲሆን፣ ይህ ሽልማት የላቀ ጥራት ያለው አካዴሚያዊ ልዕልናን፣ አዎንታዊውን የሰው ልጅ ግንኙነት እና የማህበረሰብ ማዳረስ/ግንኙነትን ላዳበሩ ለMCPS ርእሰመምህራን እውቅና/ሽልማት ይሰጣል። እንደነዚህ ዓይነት ልዩ ጥራት/ብቃት፣ በ1988 ባረፈው፣ በማርክ ማን/Mark Mann፣ የፓርክላንድ ጁኒየር ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት/Parkland Junior High School ርእሰመምህር፣ በአርአያነት የታዩ ነበሩ። ባለፉት አመታት የተደረጉ ጥቆማዎች መደገም ይችላሉ። **የጊዜ ገደብ፡-**
**4 p.m. ዓርብ፣ ጃኑዋሪ 4/2019**

**ድጋፍ ሰጪ አገልግሎቶች የዓመቱ ሠራተኛ**
ለ MCPS ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉ የድጋፍ አገልግሎቶች ሠራተኞች ለ 2019 የዓመቱ ሠራተኛ የእጩዎች ጥቆማ እየተቀበልን ነው።

አሸናፊ ሰራተኛ "Education Works Because We Do (ትምህርት ይሰራል እኛ ስለምንሰራ)" የሚለውን መፈክር በተግባር ማሳየት አለበት። ሽልማቱ የሚሰጠው በ SEIU Local 500 ነው።

ተሰያሚዎች ቋሚ ሰራተኞች መሆን አለባቸው በ MCPS የሶስት አመት አገልግሎት እንዲኖራቸው ያስፈልጋል። ዕጩዎቹ በተለያዩ መስፈርቶች ማጣሪያ ይደረጋል/ይዳኛሉ፣ የሚያካትተውም፡- ተነሳሽነት/ትጋት፣ የፈጠራ ችሎታ፣ ጥበብ እና የዓላማ ፅናት፣ ለተማሪዎች፣ ለሠራተኞቸ እና/ወይም ለአጠቃላይ ማህበረሰቡ ያደረገው/ያደረገችው አስተዋጽኦ፣ አክብሮት እና አድናቆት፣ የአመራር ብቃት፣ እና ከሰዎች ጋር አብሮ የመስራት ጥበብ/ክህሎት።

ተቀባይ የ$1,000 ጥሬ ገንዘብ ሽልማት ይቀባላል/ትቀበላለች። ሽልማቱ በሚያዝያ ወር የልጆች ሻምፒዮና ክብረ በዓል ላይ ይሰጣል።

**የስያሜዎች የጊዜ ገደብ ሀሙስ፣ ዲሰ.20 በ5 p.m. ነው።** የመሰየሚያ/መጠቆሚያ ቅጽ [እዚህ]() ይገኛል።

ጥቆማዎቹ የሚላኩት ለ፡- Ruth Musicante, SEIU Local 500, 12 Taft Court, 2nd Floor, Rockville, MD 20850 ነው።

## የዊንተር አየር፡- ከMCPS ጋር ሁልጊዜ ይገናኙ

የዊንተር አየር እየተቃረበ ነው። በአደገኛ አየር ሁኔታ ምክንያት ስለ ት/ቤት ስለሚዘጉባቸው፣ ዘግይተው ስለሚከፈቱበት እና ተማሪዎች አስቀድመው ስለሚለቀቁባቸው ወላጆች የሚማሩባቸው MCPS የተለያዩ መንገዶች ያቀርባል።

- **ከ MCPS-ማስጠንቀቂያ (AlertMCPS)**

ከአየር-ጋር-የተያያዙ የአስቸኳይ ሁኔታዎች እና በት/ቤት ስርአት ተፅእኖ በሚያደርጉ ሌሎች አሳሳቢ ክውነቶች ወቅት የቴክስት መልእክቶች ወይም ኢሜይሎች ከMCPS ተቀበሉ። ወላጆች በተለይ የልጆቻቸውን ት/ቤቶች የሚመለከቱ ማስጠንቀቂያዎች ለመቀበል በኮምፒውተር መመዝገብ ይችላሉ።

[AlertMCPS ይመዝገቡ]()

- **MCPS መነሻ ድረ-ገፅ**

[www.montgomeryschoolsmd.org](http://www.montgomeryschoolsmd.org)

- **የ QuickNotes የኢሜይል ዜና አገልግሎት**

ይመዝገቡ፡- [www.mcpsquicknotes.org](http://www.mcpsquicknotes.org)

- **የ MCPS ኬብል (ቲቪ) ቻነሎች**

Comcast 34፣ Verizon 36 ወይም RCN 89

- **የተዘገበ/የተቀዳ መረጃ**

301-279-3673

- **MCPS ን ይጠይቁ**

301-309-6277 ሰራተኞች ከሰኞ እስከ ዓርብ ከ7:30 a.m. እስከ 5:30 p.m በእንግሊዝኛና ስፓኒሽ ጥሪ ይቀበላሉ።

- **Twitter**

http://twitter.com/mcps

- **ያካባቢ ሬድዮና ቲቪ ጣብያዎች**

የአስቸኳይ ጊዜ መገናኛ መረጃዎች በልጅዎ ት/ቤት ማህደር ወቅታዊ መሆኑን እባክዎ ያረጋግጡ።

የ MCPS አስቸኳይ ሁኔታ መረጃ አቀባበል

**የላቲኖ/Latino፣ አዥያውያን/Asian ቤተሰቦች ወላጆች በሚሳተፉባቸው ዝግጅቶች እንዲገኙ ተጋብዘዋል**
ለላቲኖ/Latino እና ኤዥያ/Asian-አሜሪካውያን ቤተሰቦች የማህበረሰብ የመረጃ/ኢንፎርሜሽን ልውውጥ ስብሰባዎች የተዘጋጁት በዚህ ወር ወደ መጫረሻ ላይ ነው።

የላቲኖን ማህበረሰብን በተሻለ መንገድ ማገልገል ላይ ያተኮረ የማህበረሰብ መድረክ ሰኞ፣ ህዳር/November 26 ከ 5: 30-8:30 p.m በ Gaithersburg መካከለኛ ት/ቤት ይካሄዳል። በዋናነት ተናጋሪው እንግዳ ሱፐርኢንተንደንት ጃክ ስሚዝ/Superintendent Jack Smith ናቸው።

ይህ መድረክ የሚካሄደው ከልጆቻቸው ትምህርት እና ከቤተሰቦቻቸው ጋር ተያያዥነት ባላቸው ጉዳዮች ላይ ከላቲኖ ቤተሰቦች የሚቀርቡትን አስተያየቶች ለመስማት ነው። ተማሪዎች እና ወላጆች በት/ቤት እንዴት ምቾት እንደሚሰማቸው ለማድረግ እንደሚቻል፣ በምንባብ እና በሒሳብ መገልገያዎች/ሪሶርሶች እንዴት ልጆችን ለመርዳት እንደሚቻል፣ እና ሲስተሙ ልጆችን ለወደፊት ለማዘጋጀት እንዴት ማዘጋጀት እንደሚችል በመሳሰሉት ርእሶች ዙርያ ወላጆች በበርካታ ቡድኖች ተከፋፍለው ውይይቶች ይካሄዳሉ። የመድረኩ ውይይት የሚካሄደው በእንግሊዝኛ እና በስፓንሽ ቋንቋዎች ነው።

ይህንን ክስተት የሚያስተናግዱት Latino Student Achievement Action Group (LSAAG)፣ the Montgomery County Latino Advocacy Coalition (MCLAC) እና MCPS ናቸው።

የጌትስበርግ መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት የሚገኘው አድራሻ:- 2 Teachers' Way in Gaithersburg ነው። የልጆች እንክብካቤ ይሰጣል፣ እና የመናፈሻ ዝግጅቶችም ይኖራሉ።

እዚህ ይመዝገቡ/RSVP here።

የኤዥያ ፓስፊክ አሜሪካውያን የወላጆች ተሳትፎ ምሽት ረቡዕ ኖቨምበር 28 ከ 6-9 p.m በኸርበርት ሁቨር መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት/Herbert Hoover Middle School ይካሄዳል። ዶ/ር ስሚዝ (Dr. Smith) ቤተሰቦችን እንኳን ደህና መጣችሁ ይሏቸዋል። ስለካውንስሊንግ አገልግሎቶች፣ ስለማግኔት ት/ቤት የምልመላ ሂደት፣ በአካባቢ ትም/ቤት ፕሮግራሞች ላይ ጥብቅ እና ተገዳዳሪ ትምህርቶች እና MCPS በጨረፍታ በተሰኙ ርዕሶች ላይ የቡድን ውይይቶች ይሰጣሉ።

ይህ ሁነት የሚካሄደው በ Asian Pacific American Student Achievement Action Group (APASAAG)፣ Chinese American Parent Association፣ Montgomery County (CAPA-MC)፣ League of Educators for Asian American Progress (LEAAP)፣ እና MCPS ድጋፍ ነው።

አድራሻ፡- Herbert Hoover Middle School, 8810 Postoak Road in Potomac

እዚህ ይመዝገቡ/RSVP here።